ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ጁማዳ አልኡላ 6/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚኒስቴር ዲሴምበር 10/2021 ግ.

# አጥፊነትን መዋጋት ሃይማኖታዊ፣ ብሄራዊና ማህበራዊ ሀላፊነት ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَلا تَبْغِ الْفَسَادَ فِي الأَرْضِ إِنَّ اللَّهَ لا يُحِبُّ الْمُفْسِدِينَ}

ለአለው ለዓማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጹዋ ትርጉም፡ (በምድርም ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ፡፡ አላህ አጥፊዎችን አይወድምና) ማለት ነው፡፡

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል

አጥፊነት ለግንባታና ልማት ከፍተኛ እንቅፋት የሚሆን የግለሰቦችንና የሀገራትን ሃይሎች የሚያወድም አሉታዊ ገጽታ ነው፡፡ በመሆኑም መለኮታዊ ሃይማኖቶች የማንኛውንም አጥፊነት ገጽታ አደገኛነት በአንድ አቋም አስጠንቅቀዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በነብዩ ሷሊሕ ልሳን (ዐ.ሰ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَا تَعْثَوْا فِى الْأَرْضِ مُفْسِدِينَ}

(አመጠኞችም ኾናችሁ በምድር ላይ አታበላሹ)፡፡ እንድሁም በነብዩ ሹዓይብ ልሳን (ዐ.ሰ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَا تَبْخَسُوا النَّاسَ أَشْيَاءَهُمْ وَلَا تَعْثَوْا فِى الْأَرْضِ مُفْسِدِينَ}

(ሰዎችንም ምንም ነገራቸውን አታጉድሉባቸው፡፡ በምድርም ውስጥ አጥፊዎች ሆናችሁ አታበላሹ፡፡) አሁንም በነብዩ ሙሳ ልሳን (ዐ.ሰ.) እንድህ ይላል፡

{وَأَصْلِحْ وَلَا تَتَّبِعْ سَبِيلَ الْمُفْسِدِينَ}

(አሳምርም የአጥፊዎችንም መንገድ አትከተል) አሁንም እንድህ ይላል፡

{وَلَا تَعْثَوْا فِى الأَرْضِ مُفْسِدِينَ}

(አመጠኞችም ኾናችሁ በምድር ላይ አታበላሹ)፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ብለዋል፡ (ከአላህ ዘንድ ምንዳን የፈለገ፣ መሪን የታዘዘ፣ ከወድ ገንዘብ ምጽዋት የሰጠ፣ ለአጋሩ ገራገር የሆነና ከአጥፊነት የታቀበ ሰው እንቅልፉም ንቃቱም ሁሉም ለሱ ምንዳ ያለው ጊዜ ይሆንለታል)፡፡

አጥፊነት የተለያዩ ገጽታዎች አሉት፡፡ እጅግ አደገኛ የሚባሉት የህዝብን ንብረት በማባከን፣ የሥራ ግደታን ባለመወጣት፣ ወገንን በማስቀደም፣ በጉቦና በማምታታት አማካይነት የሚከሰቱት የገንዘብና የአስተዳደር ፍንገጣዎች ናቸው፡፡ ይህ ሁሉ የእርም ገንዘብ ማካበትና የሰዎችን ገንዘብ በከንቱ የሙብላት ዓይነት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلَا تَأْكُلُوا أَمْوَالَكُمْ بَيْنَكُمْ بِالْبَاطِلِ}

(ገንዘቦቻችሁንም በመካከላችሁ በከንቱ (ያለ አግባብ) አትብሉ፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የአላህ አርግምን በጉቦ ሰጭና ጉቦ ተቀባይ ላይ ይሁን) እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (የአላህን

ገንዘብ ያለ ሙብት አገልግሎት የሚያውሉ ሰዎች አሉ፡፡ እነሱ በትንሳኤ ቀን የእሳት ቅጣት ይጠብቃቸዋል)፡፡ እንድሁም እንድህ ይላሉ፡ ( በእርም ገንዘብ ያደገ ስጋ ገነት አይገባም፡፡ የሱ ቦታው እሳት ነው)፡፡ አሁንም እንድህ ይላሉ፡ (ያታለለን ሰው ወገናችን አይደለም)፡፡

አጥፊነትን መዋጋት ሃይማኖታዊ፣ ብሄራዊና ማህበራዊ ሀላፊነት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ሃይማኖታዊ ሀላፊነት ስንል መንፈስን መግራት፣ አላህን በመፍራትና በግልጽም ሆነ በድብቅ እሱ እንደሚቆጣጠራት እንድትገነዘብ ማድረግ ማለችን ይሆናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنْتُمْ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ}

(እርሱም የትም ብትኾኑ ከእናንተ ጋር ነው፡፡ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው፡፡) እንድሁም ይላል፡

{إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلَيْكُمْ رَقِيبًا}

(አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና፡፡)

በመንፈስ ውስጥ እውነት፣ ታማኝነት፣ ቃልን ማክበርና ሌሎችንም መልካም እሴቶች ማስረጽ የሁሉም ምእምናን ግዴታ ነው፡፡ እውነተኛ ሙእሚን የሚያጠፉ ሳይሆን የሚያበጅ ነው፡፡) አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{أَمْ نَجْعَلُ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ كَالْمُفْسِدِينَ فِي الْأَرْضِ أَمْ نَجْعَلُ الْمُتَّقِينَ كَالْفُجَّارِ}.

(በእውነቱ እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችን የሠሩትን በምድር ውስጥ እንደሚያጠፉት እናደርጋለን? ወይስ አላህን ፈሪዎቹን እንደ ከሓዲዎቹ እናደርጋለን?)

ብሄራዊ ሀላፊነት ማለት ደግሞ ለሀገር ታማኝነትና የሀገር ፈፍቅር እሴቶችን ማጠናከር፣ ለህዝብ ንብረትና ለህዝብ መገልገያዎች ያለውን

ሀላፊነት ማስረጽ፣ በመላ ማህበረሰቡ የግልጽነትና የንጹኑነት ባህልን ማስፋፋት እንድሁም የአጥፊዎችና አፍራሾችን እጅ መያዝን ያካትታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በምድር ጥፋት የሚያስፋፉ ወገኖችን ከፍተኛ ቅጣት እንደሚያደርስባቸው እንድህ በማለት አስጠንቅቋል፡

{إِنَّمَا جَزَاءُ الَّذِينَ يُحَارِبُونَ اللَّهَ وَرَسُولَهُ وَيَسْعَوْنَ فِي الْأَرْضِ فَسَادًا أَن يُقَتَّلُوا أَوْ يُصَلَّبُوا أَوْ تُقَطَّعَ أَيْدِيهِمْ وَأَرْجُلُهُم مِّنْ خِلَافٍ أَوْ يُنفَوْا مِنَ الْأَرْضِ ذَٰلِكَ لَهُمْ خِزْيٌ فِي الدُّنْيَا وَلَهُمْ فِي الْآخِرَةِ عَذَابٌ عَظِيمٌ}.

(የእነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚዋጉ በምድርም ላይ ለማጥፋት የሚተጉ ሰዎች ቅጣት መገደል ወይም መሰቀል ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከአገር መባረር ነው፡፡ ይህ በነሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት ነው፡፡ በመጨረሻይቱም ለእነርሱ ከባድ ቅጣት አላቸው፡፡)

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

የማህበራዊ ተጠያቂነት ስንልም አጥፊነትን የሚቃወሙ አጠቃላይ እሴቶችን ማጠናከር፣ በመላው ማህበረሰቡ አጥፊነት ሊያደረሰው የሚችለውን አደጋ በንቃት የሚጋፈጡ ወገኖችን የክትትል ሥራ ማጎልበትና ለዚህ ጉዳይ እገዛ የሚያደርጉ ሃይማኖታዊ ትምህርታዊና የሜዲያ ድርጅቶችን መስተጋብር ማስፋት የሚሉትንም ጉዳዮች ያካትታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{فَلَوْ لا كَانَ مِنَ الْقُرُونِ مِن قَبْلِكُمْ أُوْلُوا بَقِيَّةٍ يَنْهَوْنَ عَنِ الْفَسَادِ فِي الأَرْضِ إِلَّا قَلِيلًا مِّمَّنْ أَنجَيْنَا مِنْهُمْ}

(ከእናንተም በፊት ከነበሩት ከክፍለ ዘመናት ሰዎች ውስጥ በምድር ላይ ከማበላሸት የሚከለክሉ የመልካም ቀሪ ሥራዎች ባለቤቶች ለምን አልነበሩም ግን ከእነሱ ያዳንናቸው ጥቂቶቹ (ከለከሉና ዳኑ)፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَمَا كَانَ رَبُّكَ لِيُهْلِكَ الْقُرَى بِظُلْمٍ وَأَهْلُهَا مُصْلِحُونَ}.

(ጌታህም ከተሞችን ባለቤቶቻቸው መልካም ሠሪዎች ሆነው ሳሉ በመበደል የሚያጠፋቸው አልነበረም፡፡)

በመላ ማህበረሰቡ መረጋጋት እንዲሰፍንአጥፊን አለመደበቅና ማንኛውንም የጥፋት ዓይነት ለማጋለጥ ከፖሊስ ጋር መተባበርም በዚሁ ዘርፍ ይካተታል፡፡ ንብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡፡

(የአላህን ወሰኖች የሚያከብርና እነዚህን ወሰኖች የሚዳፈር ሰው ምሳሌ በአንድት መርከብ ላይ ተሳፍረው እጣ ተጣጥለው ከፊሎቹ የላይኛው ክፍል ከፊሎቹ ደግሞ የታችኛው ክፍል እንደደረሳቸው ሰዎች ዓይነት ነው፡፡ በታችኛው ክፍል ያሉት ሰዎች ውሃ ለማግኘት ሲፈለጉ በላኛው ክፍል በሰፈሩት ሰዎች ላይ ማለፍ ነበረባቸው፡፡ እኛ ሰዎችን ከማስቸገር በቦታችን ቀዳዳ ብናወጣ ከበላያችን ያሉትን ሰዎች አናስቸግርም ነበር የሚል ሀሳብ መጣላቸው፡፡ ያሰቡትን እንዲፈጽሙ ከተዋቸው ሁላቸውም ያልቃሉ፡፡ አጃቸውን ቢይዙ ግን ያድኗቸዋል እንድሁም ሁላቸውም ይድናሉ)፡፡

ጌታችን ሆይ! ግብጽንና የዓለም ሀገራትን ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን አሚን፡፡